**መለስ ዜናዊ በአዘጋጀልን የጥፋት ቦይ እንደዋዛ እየፈሰስን ዳግም ከማንመለስበት ማህበራዊ አዘቅት ጨርሰን እንዳንዋጥ ካለንበት ቆም ብለን ደጋግመን እንድናስብ ጥሪዬ፤**

# ይድረስ

በትልቁ ለማከብራችሁ በትግራይ ክፍለ-ሃገር የተወለዳችሁ ኢትዮጵያዊ ወገኖቼ፤ በምትገኙበት አድራሻ ሁሉ፣ወንድማዊ ሰላምታየ ይድረሳችሁ።

እንደ ኢትዮጵያዊ፥ በትዉልድ ተረኛነታችን ዘመን ላይ በገጠመን በዚህ ዉስብስብና አስከፊ የፖሊቲካና ማህበርዊ አዘቅት እንደመገኘታችን፤በፍጥነት ካአለንበት ቆም ብለን በጥልቀት ታሪካችን መመርምርና የዛሬን እኛነታችን በማገነዘብ በጋራ መፍትሔ መፈለግ እንደለብን በጥብቅ አምናለሁ።

ማንኛችንም አበክረን እንድምናውቀው የገናናዋ ሃገራችን አኩሪ የርጅም ጊዜ ስልጣኔ ማስርጃችን፤ በሕግ የሚመራ ዘመናዊ መንግስት የማደራጀትና ከብሉይ ኪዳን ጀምረን ወግና ስርዓት ያለው እምነት ያለን ስለመሆኑ የበዛው ማአስረጃችን ባክሱም የሚገኝና ባክሱም ዘመነ መንግስት የተከናወነ ነው። በሁላም ቢሆን እኛ ኢትዮጵያዊአን በልዩነትም ተከባብሮ መኖር የምንችል፤ ለሰዉ ልጅ ሰዉነት መከብርን ቅድምያ የመስጠት ባሕል እንዳለን ቀደምት ወገኖቻችን ያስመሰከሩት፥ በዚሁ በትግራይ ዉስጥ የነብዩ ሙሃመድ ተከታዮች ሰውነታቸዉን አክብረው ተቀብለው ባስተናገዱበት ጊዜ ነበር። በዚህ በጎ ምግባር ስሜታቸዉ የተነካዉ ነብዩም፤ ለተክታዮቻቸው እትዮጵያን የማክበር አድራ ጥለው እንዳለፉ ይተረካል።

ይህንና ሌላም ያአባት አደራ፥ ውርሰ የታሪክ ዕዳን በመወጣት ክብራችንም ጠብቆ በማቆየት የትዉልድ ተረኛ ህላፊነት በብቃት በመወጣት ረገድም ሳይታጎል እስከዚህ ትዉልድ አባቶች ድረስ ያዘልቁ ራሳቸዉን ገለዉ የታፈርች ሃገርና የኩሩ ህዝብ ታሪክ መጠኑ በገንዘብ የማይለካ በእጅጉ የሚአኮራ ሃብት አስረክበዉን ነበር።

ዛሬ እነመለስ ዜናዊን የመሰሉ መሪወች እንደ አቶ ስብሃት ነጋ የመሰሉ አማካሪወች በዚህ እድለኛ ባልሆነ ትዉልድ የከፋ ዘመን ዉስጥ ፤ ቅሌት ሃብታቸው ዉርደት ክብራቸዉ ሁኖ ለህገራችን የመከራና የጥፋት ጊዜ አዘማቾች መከራ ደጋሾች ይሁኑ እንጅ።ኢትዮጵያን ታክል ኩሩና ገናና ሀገር እጅ ከወርች የታሰረች በር አልባ ሀገር ሁና የነጅቡቲ አጎንባሽ ችሮታ ጠባቂና የባህር በር ግብር ከፍይ ጉደኛ ምዕራፍ ላይ ዛሬ ትድረስ እንጅ። “የሃገሬ የተፈጥሮ ደንበር ቀይ ባህር ነው እኔ ከሃገሬ ጥርኝ አፈር አንስቸ አሳልፌ ለመስጠት መብቱም ፍላጎቱም የለኝም” ብሎ እንደ እምነቱም ሕይወቱን ሙሉ በኩራት አስከብሮ እሱም በተራው አደራ የተወው የጉራዐውና የዶጋሊዉ አንበሳ ጀግናው ራስ አሉላ አባነጋም የበቀለው እናተ ተወልዳችሁ ባደጋችሁበት ትግራይ መሬት ነብረ። ለሃገራቸው ፍቅር አንድነትና ጥንካሬ ምንም ዐይነት ድርድር የማያውቁት ታላቁ የ ኢትዮጵያ መሪ ንጉሠ-ነግሥት አፄ ዮሐንስ አራተኛም አንገታቸውን መተማ የተሰየፉት የተውለዱት ትግራይ

ክፍለሃገር ነው። ዛሬ ያ ቅዱስ ደም የፈሰሰበት የጀግና ሕይዎት የተሰዋበትን የመተማና ቓራ ክቡር መሬት መለስ እንዳሻው በየቀኑ እየሸራረፈ ለሱዳን መንግስት እፈንልኝ ውልታ ቢሰጠውም መተማ በሌላ በኩል የዓጼ ዮሃንስ ክቡር መሰዋዕትንትም ላንድነት ለሉዐልዊነት ለተከበረ ኩሩ ሕዝብ ሞአችንታችን የምናሳይበት ማስረጃችን ነው። ዛሬ ዘመነኞች ነን በሚሉት እዉነት መናገር ፊዉዳልዊነት እንደሚአሰኝ ባውቅም የደጀዝማች ዘራይ ደረስ ና የአዋሎምም የጀግንነት ታሪክም ቢሆን ቢረሳ ህሌና ይከሳል።

ምንም የትግራይን ህዝብ ለማሳሳትና ከታሪክዊ ሃላፊንቱ ለማዘናጋት እንዲመች ተብሎ ታሪክ አስረጅወችንና የሃገር ተቆርቋሪ አባቶቻችሁቻችሁ ፊውዳል ናቸው እየትሰኙ በጭካኔ በገንዛ ልጆቻቸው እንደ ሽራሮ ባሉ ቦታውች ከባዕድ እጅ ነጥቀው ነጻ ባወጠት ሃገር በገፍ ቢጨፈጨፉም አሁንም ከሌላዉ ወገናችሁ ለይቶ ሁልጊዜ የትግራይ ወጣቶች ደማቸው የከልብ ሕይዎታቸዉም ከንቱ ሁኖ ሁልግዚኢ ወዲ ዜናውይ የሕይዎቱ እንጀራ ማብስያ ማገዶ አድርጎአችሁ እንዲችል የበሬ ወለደ ተንኮሉን የዘላለም ማሳረፊያ ሊአደርጋችሁ ምኞቱ ነው።

ውድ ወገኖቸ፤ አሁንም ደጋግማችሁ እየሆነ ያለዉን ነገር እንደታሰቡ እመክራችሁልሁ።

ትናንት እነመለስ የትግራይን ሕዝብ ዐርነት ልናወጣ ነው በሚል በዉሸት እየሰበኩ ልጆቹን ከጉያው ወስደው የሻብያ ግንባር ጦር አርገው ኤርትራን አስገነጠሉ የባሕር በርሕ ተዘጋ እንጅ መለስ ባዘጋጀው ቦይ የሚፍሰስ እግራችሁን ሳቡትና አስቡበት። ትላንት በወንድሞቻችን የትግራይ ልጆች ሕይወት መጠነ ሰፊ መስዋዕትነት ፕሬዚዳንት ለመባል የበቁት እነአቶ ኢሳይያስ በማግስቱ ነበር አይደር ላይ ምንም በማያዉቁ ህጻናት ሕይወት ብላስተር ቦምብ የሞከሩባችው ፤ብሎም ለዝያን ያህል ግዙፍ ሰራዊት እልቂትና ንብረት ማውደም እንደበቃን ሁላችሁም ታዉቁታላችሁ ። የመንን አልፋ ትግዛ እንደነበር ታሪክ የነብራት ህገራችን ኢትዮጵያ፤ በትግራይ ልጆች የቅድምያ መስዋዕትነት ለዚህ ስልጣን የበቁት እነመለስ ዜናዊ በማግስቱ ኢትዮጵያን ባስገባሪነት ላይ የተመሰረተ ሕይወት የሚኖራት ኤርትራ ከኢትዮጵያ እንድትገነጠል ማመልከቻ ለተባበሩ መንግስታት ሲመልክቱ ያአሰብ የባህር በርም ጭምር የኤርትራ እንደሆነ መስክረው በበሕሩ ዳርቻ የሚኖረውን የአፋር ህዝብ መብት ከምንም ሳይቆጥሩ ነበር። በዚህም የእነአሉላ ሃገር እጅ ተወርች የታሰርች በሮአ የተዘጋ መፈናፈኛ ያጣች ለመሆን በቅታለች።

እነመለስ የኤርትራን ገዥዎች እትዮጵያን እየተጠቀሙ መበልጽግ ራዕይ ለማሳካት ሕልም መትግበር የሚችሉት፤ የጣልያን ፋሽሽት በመጨራሻ የጥፋት ዘመኑ ያወጣዉን በዘር ከፋፍሎ የማጥፋት ሃሳብ ተጠቅመው ህዝቡን እርስ በርስ አናክሰው አንድነቱን ሲናጉ በመሆኑ ይህን የተፈበረከ የጎሳ ፖለቲካ ፈልስፈው ያናፍሱ እንጅ፤ በዕዉነት የኢትዮጵያ ታሪክ ሁኖ ይህ በድህነት የሚማቅቅን መከረኛ ሕዝብ ለዕድገት የሚአበቃዉ ሁኖ አልነበረም። ይህም እነሱን እስከጠቀመ ድርስ የማያከብሩት የዘር ፖለቲካ ንድፈ ሃሳብ እንጅ፤ እነ ሃያሎም አራያን በግፍ አርደው እነስየን አብርሃ አስረው እያሳቃዩ እነበረክት ስሞንና ዮሴፍ ህላዌን ባዕድ ካሉት ኤርትራ ሙሉ

በሙሉ ተወላጆች ያአማራነት ሰርቲፊከት ተሰጥተው መጠን ያለፈ ብልግና አይሰሩም ነበር።

ለምንድነው ዐይንችሁን ጨፍኑ እናሞኛችሁ ስትባሉ ሕይወትን እስከሚሰጥ ማህበርዊ ህልዉናን ማሳጣት እስካለፈ የደረሰ የምትሞኙት። የወራሪ ጣልያን ጠላት አጋፋሪ ወልቃይቴው ባንዳ ደጃዝማች ጎላ አማች መለሰ እኮ ያባት አደራ የመውጣት ሃላፊነት ያለው አልነበረም።

የልጆቻችሁን ከደም መፍሰስ ያለፈ ሕይወት የሻብያ የበላይነት ማስከበሪ አድርጎ ሃገራችሁን የናደ የባሕር በር ዘግቶ እኔ ልጃችሁ እያለ በህዝብ የሚቀልድ የውስጥ አርበኛ አምናችሁ ለምን ዛሬም ትሞኛላችሁ።

<u>ዕመኑኝ፣</u> መለስ ዜናዊ እንዲህ በከፍተኛ ጥበብ ያዘውን የሰመረ የምዕራብ ዲፕሎማሲ እስከሚያሳጣው የደረሰ ሕዝብን የሚአስጨፈጭፈው የስልጣን አባዜ የሚበቃዉን ከፍተኛ ንዋይ ሳያካብት ውይም ለሌላ ምንም ነገር ሳይሆን ትልቁ ጉዳይ አብረው በየብረሃው ሲውድቁና ሲነሱ የነብሩትን እነ ገብሩ አስራትን ያስከዳዉን የሱ ትልቅ ጉዳይ የፈጠራትን አዲስ ሃገር ኤርትራን እስከዘለአለሙ ድረስ እትዮጵያን ያአስገባሪነት ሕጋዊ መሰረት ሳይፈጥር ስለመሸበት (ሕጋዊ ደንበርና የባህር በር ውል...) እንጅ ከዚህ የተለየ ትልማንና ማረት በሃገሪቱ በየጊዘው እየተለመነ የሚገባው ሰፊ መጠን ያለው ገንዘብ ተመልሶ የሚገባው ከኒዮርክ እስከ አውሮፓ የተልያዩ ባንኮቹ መሆኑ አንድ ቀን እስከ ዝርዝር ስሌቱ ለሕዝብ የሚቀርብበት ጊዜ ብዙ እሩቅ አይሆንም.አዳዲሶቹ ታምረኛ ነጋዴወች ከምንም ተነስተዉ “ በነፃዉ ገብያ ከዚህ ደረሱ “ እንዲሰኙ የሚወራላቸው ከምንም ተነስተው ሰማይ የነኩት በጣም ጥቂት አንዳ አንድ ነጋዴወችነ በታምር ሳይሆን በየትኛዉም ቦታ መንገዱ ቀና እንዲሆንላቸው የተመቻቸላቸው የመለስ ዜናዊ ትርፊ እኩል ነጋዴወች ናቸው።(ይህን ምናልባት ዛሬ ቀርቁሮት ለንስሃ ብሎ እንኮአ ቢናገር በመጀመሪያ ጨዋታ ዉስጥ እኩል ተነስቶ ሽሪኮቹን አስብልቶ በእስር የሚማቅቀዉ ታምራት ብዙ ያዉቃል)

ሌላ ማስተዋል ያለብን እነመለስ ዜናዊ የኤርትራን ማስገንጠል ብሎም ኤትዮጵያን ባህር በር አልባ የማድረግ ፍላጎታቸውን ለመተግበር ሌላዉን የ ኢትዮጵያ ሕዝብ በጎሰኛነት ፖለቲካ ማደናገር ስለነበር በሕዝብ መሃከል የነዙትን መርዝ ጉዳይ መጤን ያለበት ይመስልኛል።

እንደሚታወቀዉ ሰሜን አሜሪካ የሁሉም አለም የሰው ዘር መኖርያ እየሆነች ነው። የአሁኑ ጊዜ የዲሞክራሲ ሞዴል ስልተባለችም ማንኛዉም ሃገርና ሕዝብ በዘመናችን በውስጡ ያለውን ዲምክራሲ የሚለካው ባአብዛኛው በ ዩንይትድ ስተትስ አሜሪካ እየሆነ ባለበት ሀገር እይታየ ያለው ዲሞክራሲ በግለሰብ ነጻነትና ፍትህ ላይ ያረፈ እንጅ እንደነመለስ የግለሰብን መብት በብሄር ስሜት አደናግሮ መብቱን መቀማትና አፍኖ ለመግዛት ማደናገሪያ ያለበት አይደለም። ቃንቃ ከመገናኛ መሳሪያነት ዉጭ ፋዪዳ ያለው ይመስል በወገኑ ሕይወት ቁማር የሚጫወተው ከሃዲዉና ጨክኙ  እቶ መለስ ቃንቃችሁ ሌላም ሌላ እያለ በየጊዜው የሚአደናግረውን ልትመረመሩትና ጠላትነቱን ልትረዱት ይገባል። እውነት አንድ ሰው

የጎሳዉን ቋንቋ ብቻ የሙጥኝ ብሎ እንዴት ከሌላው ጋር ተግባብቶ የፈለገዉን ሊአሞላ ይችላል? ይህ ክሆነ ሰው ይበልጥ በስፋት ሊገናኘው የሚአስችለዉን ለምሳሌ እንግሊዘኛ ለማወቅ ሰው ገንዘቡን ጊዜዉን የሚአባክንበት ምክንያት ምን ሊሆን ይችላል። ዕዉነተኛና ለወገኑ ሕይወት በዕድገት መለውጥ የሚፈልግ በዚህ ሰዐት፣ሓገሪቱ ከምትገኝበት የድህነት ሕይወትና እየታወታወቀች ካለችበት የተራቢነት ታሪክ ለማውጣት ሕዝብን አቀራርቦ የስራ ሰላምን ፈጥሮ በተዋሃደ ስነልቦና ድንግል የከርሰ ምድር ሃብትን ተጠቅሞ ሃገርን ለመገንባት ከመጣር ይልቅ ሰዉን በቋንቋና ባህል አራርቆ ድህነትን ማፋጠን አልነበርም።

አሁንም መለስ የፖልቲካ ኪሳራዉን በትግራይ ሕዝብ ጫንቃ ላይ ሊያሳርፈውና ሕዝቡንም እንደገና ወደሌላ የፖሊቲካ ማጥ ውስጥ ሊስገባው ይፈልጋል. ዛረም ቡዳ ዐይኑን በልጆችህ አጎርጦአል፣ ዛሬም የማያልቅበትን ዉሸት ሊቀላምድብህ ክሌላዉ ወገንህ ለይቶ እሁንም በእናንተ ደምና ላብ ዉድ ሕይወት ሌላ ጉደኛ ሁኔታ ሊፈጥር እየመከረ ነው።

ከተንኮለኛው ክሃዲዉ መለስ ዳግም ጥፋት ራስችሁን ኣድናችሁ ክወገናችሁ ጋር ባንድነት አብራ መሰሪዉን መለስንና ግብረአበሮቹን በማስወገድ እንደአብቶቻችንም ኢትዮጵያን ለልጆቻችን እንናሳልፋት እመክራለሁ። ሁሉንም ጥረታችን እግዚአብሔር ይባርክልን አሜን።

ኪዳነ ማርያም ጌታቸው።

ከጉድባ